የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 27 ቀን 2002 ዓ.ም.

# መቶኛ አመት የሴቶች ቀን ሲከበር

የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም. (ማርች 8 ቀን 2010 ዓ.ም.) የሰብዕናቸውና የትግላቸው መለያ የሆነው አለም አቀፍ የሴቶች ቀን በመላው አለም ለሴቶች መብት በቆሙ በርካታ ሕዝባዊ ድርጅቶች በተለያዩ መፈክሮችና መርሃ ግብሮች እያጀቡ ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ እንደሚያከብሩት የወጡ መግለጫዎቻቸው ይጠቁማሉ። የኢትዮጵያ ሴቶችም የአለም ሴቶች አካል ናቸውና የመለስ አገዛዝ እንደለመደበት በሱ የሙዚቃ ቃና ከበሮውን ደልቆ ለፕሮፓጋናዳ ፍጆታ መጠቀሚያ ማድረጉ ባይቀርም በሀገር ቤት የሚገኙት ታጋይ ሴቶች ግን የተሰዉ እህቶቻቸውን፣ እናቶቻቸውን፣ ሴት ልጆቻቸውንና የትግል ጓደኞቻቸውን በመዘከር ቀኑን የሚያስቡትና የሚያከብሩት እንደሆነ ግልጽ ነው። በውጭ ሀገርም ከአለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት ለምሳሌ ይህንኑ ቀን አስመልክቶ ለመዘከር የሁለት ቀን ዝግጅት ማድረጉን ከአካባቢው የደረሱ ዜናዎች ያስረዳሉ።

የዘንድሮውን አከባበር ልዩ የሚያደርገው ቀኑ በአለም አቀፍ ደረጃ መከበር ከተጀመረ መቶኛ አመቱን በማስቆጠሩ ነው። ዛሬ በብዙ ዴሞክራቲክ ሥርአት በገነቡ ሀገሮች ተክብረው ያሉ ሴት ነክ የሆኑ መብቶች እንደ ቀላልና የተለመደ ተደርገው የሚታዩት ባለፉት 100 አመታት ከፍተኛ ትግልና በርካታ መስዋዕት የጠየቁ የትግል ውጤቶች ናቸው። የመመረጥና የመምረጥ መብት በምሳሌ የሚጠቀስ ነው። ዛሬም ቢሆን በርካታ ጥያቄዎቻቸው ገና አልተመለሱምና ይህንን ቀን በሚያከብሩበት ወቅት አሁንም ያልተቋረጠ የመቀስቀስ፣ የማደራጀትና የማንቃት ትግል ማድረግ ግዴታቸው መሆኑን ከግንዛቤ እያስገቡ ናቸው።

የሴቶች ጥያቄ በጣም ወሳኝ በመሆኑ የዴሞክራሲ ሥርአት በተመሰረተበት ሀገር ሳይቀር ለእኩል ሥራ እኩል ደሞዝ" ፣ „ቁልፍ በሆኑ የሥልጣን ቦታዎች መመደብ"፣ „በቂ የወሊድ እረፍት መኖር"፣ „በሙያቸው መስክ እየሰሩም የቤተሰብ ኃላፊነታቸውን

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

እንዲወጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት"፣ „በቂ የሕፃናት ማሳደጊያ ቦታ ማዘጋጀት"፣ የመሳሰሉት በተደጋጋሚና ተዘውትረው የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም ዛሬ መቶኛ አመት ያስቆጠረውን አለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሲከበር በአለም አካባቢ በየሀገሮቻቸው ሴቶች እያነሱ ያሉ ጥያቄዎችን አስመልክቶ ምን ደረጃ ላይ ነን?፤ ምን ተሰራ?፤ ምን ውጤት ተገኘ? ፤ ምንስ ቀርቷል?፤ ያልተሰሩበት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች ጠለቅ ያለ ግምገማ የሚያደርጉበት፣ መፍትሄ የሚያፈላልጉበትና ተመክሮም የሚለዋወጡበት መድረክ ነው።

የትኛውም ሕብረተሰብ ይሁን፣ ጤናማ ለሆነ የዜጎቹ ግንኙነት፣ ለማህበራዊና ለኤኮኖሚ እድገቱ የሴቶች ጥያቄ በተገቢው ሁኔታ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል። ሴቶች የነጻነት መብታቸውን ባልተጎናፀፉበት ጤናማ የፖለቲካ ሥርአት ሰፍኗል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን የኢትዮጵያ ሴቶችን ሁኔታ ስንመለከትም በፖለቲካው(በውሳኔ ተሳትፎ)፤ በኤኮኖሚው(ለእኩል ሥራ እኩል ደሞዝ)፣ በማህበራዊ(የፆታ እኩልነት) ብቻ ሳይሆን በፆታቸውም ለአስፀያፊ ጭቆና የተዳረጉ ናቸው። ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የሚያድጉት የወንድ የበላይነት ሰፍኖ ባለበት ሕብረተሰብና ምህዳር ውስጥ ነው። ለጠለፋ፣ ለአስገድዶ መድፈርና ድብደባ ለመሳሰሉት የወንጀል ተግባራት የተጋለጡ ብቻ ሳይሆኑ በስፋትም የሚጠቁም ጭምር ናቸው። ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሴቶች ዘመናዊውን ትምህርት የቀመሱት ጭምር ቤተሰብ ሲመሰረቱ ለትዳራቸው መጎልበት የራሳቸው መተዳደሪያ ገቢ የሌላቸው በመሆናቸው የጥገኝነት ስሜት የሚያሳድርባቸው ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ለሚኖር አለመግባባትም የራሱ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሚገኝ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

ማህበራዊ ቀውሶች መፍትሄ ባላገኙበትና ይበልጡንም ወያኔ በሚከተለው ጎጠኛ ፖሊሲ እየተባባሱ በሚሄዱበት በሀገራችን የዚህ ገፈት ቀማሽና የቀውሱ ሰለባ እየሆኑ ያሉት ሴቶችና ሕፃናት መሆናቸው በበርካታ ጥናቶች የተረጋገጠ ነው። ትውልድ መታሪ በሆነው የኤድስ በሽታ ከተለከፉት ዜጎቻችን መሃል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። ሳንባ ነቀርሳም ሆነ ሕገወጥ ፅንስ ማስወረድ ሳቢያ ዛሬም ቢሆን የለጋ ወጣት ሴቶችን ሕይወት ከሚቀስፉት ውስጥ ናቸው። በድህነትና በሱም ሳቢያ የጤና አገልግሎት ባለማግኘትም ያለ እድሜ ሕይወታቸው የሚያልፈው በርካታ ናቸው። የትምህርት እድል የማግኘት ጠባብ መሆንና በማህበራዊ ኑሮ መጎሳቀል በሴቶች ላይ የበለጠ ነው። የወጣት ሴቶች መንገድ አዳሪነትና ለወሲብ ባርነት፣ በአደንዛዥ ዕጸዋት ሱስ መውደቅ፣ ለወንዶች ብዝበዛና ዋልጌነት መዳረግ፣ ለድብደባና ጨካኝ ቅጣት ጭምር መጋለጥና ቀኑን እየጠበቀ በሚመጣው ረሃብና ችግር በብዛት ሰለባ እየሆኑ ያሉት ሴቶች ናቸው። አሁንም ድረስ ጎጂ ባሕሎች በሕግ የመጠየቃቸው ሁኔታ በባህል ማክበር ምክንያት እየተሳበበ ሕጋዊ እርምጃ አይወሰድም። ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ወጣት ልጃገረዶችን መጥለፍና አስገድዶ መድፈር ዛሬም ያለ ነው።

ታዲያ የሴቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ ባጭሩ ይህን ሆኖ ሳለ የመለስ አገዛዝ የሴቶችን እኩልነት በተግባር የሚያረጋግጥ በሕገ መንግሥቱ አስፍሬያለሁ እያለ ቢመጻደቅም ከ18 አመት በኋላም ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየው የመብት መከበርን ሳይሆን በበለጠ መገፈፍን ነው። በአገዛዙ በኩል ለሴቶች ሁኔታ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት በሁሉም መስክ ያላቸው ተሳትፎ ከወንዱ ጋር ሲነጻጸር እጅግ ወደኋላ

የቀረ ነው። እጅግ በጣም በጣት የሚቆጠሩ የአገዛዙ አባላት የሆኑ ሴቶች እዚህም እዚያም በመካከለኛ የሥልጣን ቦታ ስለተቀመጡ ብዙሃኑ ሴቶች ከመድረኩ ተገለውና ተጨቁነው መገኘታቸውን አይሸፍነውም። የደርግ አገዛዝን ለመጣል በተደረገው ቆራጥና የመረረ ትግል በብዛት ተሳትፏቸውና ተጋድሏቸው አኩሪ ታሪክ ቢያስመዘግቡም እናቶቻችን፣ እህቶቻችን፤ ሚስቶቻችን ወጣት ሴቶቻችን የትግል ፍሬያቸውን ለማየት አልታደሉም።

ስለሆነም ሴቶች ትግላቸውን ቀጥለው ይገኛሉ። አሁንም መታገል፣ መሰዋዕት መክፈል፣ መታሰር፣ መገደል፣ መሰደድ አልተለያቸውም። ጉልበታቸው መበዝበዝ፣ ስብዕናቸው መደፍር፣ ክብረ ሕሊናቸው መሳቀቅ አልቀረላቸውም። ታጋይ ሴቶች ደብዛቸው እንዲጠፋ መደረጉ አሁንም አላቆመም። ከ1993 ዓ.ም. ጀምሮ መዳረሻዋ ያልታወቀው እውቋ የኢሕአፓ ታጋይ አበራሽ በርታ የዚሁ አገዛዝ ሰለባ ነች። ብርቱካን ሚደቅሳ ታስራ ከተፈታች በኋላ ዳግም ለእስር ተዳርጋ በቃሊቲ እየማቀቀች ትገኛለች። እነዚህ ለአብነት ተጠቀሱ እንጂ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሚገኙ ማጎሪያዎች ታስረው መግለጫ በማይገኝለት አረመኔ አገዛዝ እየተሰቃዩ ያሉ ሴቶች ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ ነው። የመለስ አገዛዝ ስለ ሴቶች እኩልነት፣ ያላወራው፣ ያልፃፈው፣ ያልለፈለፈው ፕሮፓጋንዳ፣ ያልወሰደው ውሳኔ የለም። የነጻነት መብታቸውን ስላልተጎናጸፉ ግን ለሴቶቹ ጠብ ያለ ነገር የለም። ከከፋ ድህነት ለመገላገል የሚያስችላቸው የፖለቲካ ሥርአትና ምህዳር አላገኙም።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው የሴቶች ጥያቄ ለሰብአዊና ዴሞክራሲ መብቶች መከበር ከሚደረገው ትግል ጋር በጥብቅ የተያያዘ መሆን ብቻ ሳይሆን የፆታ እኩልነታቸውን ከልብ በማይፈልግ ኋላቀር ሥርአት መበደላቸው እንዲያከትም ለዚህ ሁኔታ ዋና ተጠያቂ የሆነው የመለስ አገዛዝ መወገድ አማራጭ የሌለው መሆኑን ነው። ስለዚህም „የሴቶች መብት ይከበር፣ እኩልነታቸው ይረጋገጥ፣ የሥልጣን ባለቤት ይሁኑ ብሎ መታገል ዛሬም ወቅታዊ ሆኖ ይገኛል። ዛሬ ይህን አለም አቀፍ የሴቶች መቶኛ አመት ቀን ሲከበር ንቁ ዜጋ ነኝ፣ የሀገሬም ጉዳይ ያገኛል፣ የሴቶች ጉዳይ በቀጡ ይመለከተኛል የሚሉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በዝግጅታቸው ተካፋይ በመሆን በአላቸውን ሊያደምቀው፣ ትግላቸው ስምሪት እንዲያገኝ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክት ኢሕአፓ ጥሪውን ያቀርባል። ኢሕአፓ የሴቶች መብት ይከበር ሲል ለተራ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ መጠቀሚያ ሳይሆን ከልብ የሚያምንበት ለመሆኑ በአባልነት ተሰልፈው ሲታገሉ የተሰዉ፣ የቆሰሉ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሁሉና አሁንም በአባልነት ግዳጃቸውን እየተወጡ የሚገኙ ሴት አባላቱ የሚመሰክሩት ነው። ያለ ሴቶች ተሳትፎ ትግሉ ግቡን አይመታም ሲልም ይህንን ሁሉ ከግንዛቤ በማስገባት ነው። ኢሕአፓ ሴቶች በሚያደርጉት ሁለገብ ትግል ምንግዜም ከጎናቸው ሲሆን ድጋፉንም በአክብሮት እየገለጸ ነው። እንኳን ለመቶኛ በአል አከባበር አደረሰን። የትግልና የድል ጎዳና እንዲከፍትም ልባዊ ምኞቱን ኢሕአፓ ያተላልፍላችኋል።

የሴቶች ትግል ይለምለም!!